የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት

Catering and Tourism Training Inistitute



6ኛው ቱሪዝምና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት
ከግንቦት 5-9 2010

Tourism and Hospitality week
May 12-16 2018

# “ሰላም ለቱሪዝም” ዘላቂ የቱሪዝም ልማት ለህዳሴያችን

ቅጽ 1
ቁጥር 1
ግንቦት 2010 ዓ.ም

## ተልዕኮ

በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ተገቢውን ስልጠና በመስጠት ብቁ የሰው ኃይል ማፍራት፣ ጥናትና ምርምር በማካሄድ ኢንዱስትሪውን ማሳደግ፣ የማማከር አገልግሎት በመስጠት የአሰራር ጥራትን ማሻሻል እና ሃገሪቱ ከዘርፉ ተጠቃሚ እንድትሆን ማስቻል፡፡

## ራዕይ

በላቀ ስልጠና፣ በምርምር እና በማማከር አገልግሎት በ2017 በአፍሪቃ ከሚገኙ 5 ቀዳሚ የሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ተቋማት መካከል አንዱ መሆን፡፡

## እሴቶች

* ብዝሀነትን ማክበር
* እንግዳ ተቀባይነት
* ግልጽነት
* ተጠያቂነት
* ለለውጥ ዝግጁነት
* የላቀ አገልግሎት
* አሳታፊነት
* ፍትሃዊነት
* እኩልነት
* ፈጣሪነት





## ማውጫ

| | |
|---|---|
| ራዕይ፣ ተልዕኮ፣ እሴቶች | VI |
| የአዘጋጆች መልዕክት | VII |
| መልዕክቶች | 6 |
| የተቋሙ ታሪካዊ አመሰራረት | 12 |
| የተቋሙ አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴዎች | 13 |
| የሀገራችን የቱሪዝም እድገት ለስራ እድል ፈጠራ | 24 |
| የእንግዶች አምድ | 30 |
| አመታዊ ሁነትና ፋይዳዎቹ | 34 |
| የመዝናኛ አምድ | 42 |
| ዜና ፎቶ | 48 |


**አዘጋጆች : ብሩክ ታደሰ**
**ታረቀኝ መኮንን**
**መሰረት ታምር**

**አድራሻ፡-**
**በባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር**
**የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት (ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ.)**

**ከሜክስኮ ወደ ቄራ በሚወስደው መንገድ ገነት ሆቴል አጠገብ**

ስልክ: +251 11 833 4213/16
Email cttipir@gmail.com
Website: www.cttiedu.org
Facebook CTTI PIR
Twitter CTTI
P. O. Box 4350 (Addis Ababa)







የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
Catering and Tourism Training Inisitute

# የአዘጋጆች መልዕክት

*የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት(ሆ.ቱሥ.ማ.ኢ.)በሀገራችን የሆቴልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪ እንዲፈነጥቅ ፋና ወጊ የሆነ የመጀመሪያው የመንግስት ተቋም ነው፡፡ ይህ ተቋም ከተመሠረተበት ከ1961 ዓ.ም ጀምሮ ላለፉት 49 አመታት እንዱስትሪው የሚፈልገውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በማሰልጠንና በማቅረብ በሀገራችን በመሪነት ከሚገኙት የአገልግሎት ዘርፎች አንዱ የሆነውን የሆቴልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪ የላቀ አስተዋፅኦ እያበረከተ የሚገኝ ተቋም ነው፡፡*

*ይህ አንጋፋና ፋና ወጊ የማሰልጠኛ ተቋም መንግስት በሰጠው ልዩ ትኩረት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 174/2002 ዓ.ም በአዲስ መልክ ተቋቁሞ ተገቢውን ትምህርትና ሥልጠና፣ ጥናትና ምርምር እና የማማከር አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡*

*የህዝብና አለም አቀፍ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት በተቋሙ ከሀገር ውጭና ከሀገር ውስጥ ግንኙነት አንፃር የተለያዩ ስራዎችን በመስራት እንዲሁም በኤሌክትሮኒክስና በህትመት ውጤቶች ተቋሙን በማስተዋወቅ የገፅታ ግንባታና የጋራ መግባባት ስራዎችን በበቂ ሁኔታ ለማከናወን እየሰራ ነው፡፡ ይህን መጽሔት በየዓመቱ የሚከበረውን የቱሪዝምና እንግዳ ተቀባይነት (Hospitality) ሳምንት ሁነትን ምክንያት በማድረግ እንደተቋም የተከናወኑ ተግባራትን በከፊል መረጃ ለመስጠት፣ አስተማሪና እያዝናኑ ቁምነገር የሚያስጨብጡ ርዕሰ ጉዳዮችን በማካተት ከሌሎች ባለሙዎች ጋር በመሆን አዘጋጅቷል፡፡*

*በመሆኑም አንብባችሁ ለምትሰጡን ገንቢ አስተያየት በቅድሚያ እያመሰገንን ለመፅሄቱ ዝግጅት ስኬት እገዛ ላደረጉልን ምስጋናችን ላቅ ያለ ነው!*

*መልካም ንባብ!*



## የክብርት ወ/ሮ መአዛ ገ/መድህን
## የቱሪዝም ዘርፍ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ መልእክት

ባለፉት ተከታታይ አስርት ዓመታት በሀገራችን የታየው አበረታች የኢኮኖሚ እድገት ለውጥ የበለጠ እንዲፋጠንና አገራችን የነደፈችውን ሁለተኛውን የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንዲሳካ አስተዋጽኦ ከሚያበረክቱት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዘርፎች መካከል የቱሪዝም ዘርፍ አንዱ ነው፡፡

ኢትዮጵያ የበርካታ ተፈጥሯዊ፤ ታሪካዊ፣ ባሕላዊና ሀይማታዊ እሴቶች ባለቤት፣ የተለያዩ ባህል፣ እምነትና ቋንቋ ባለቤት የሆኑ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በአንድነት የሚኖሩባት፣ የሰው ዘር መገኛና የስለጣኔ ምንጭ ሀገር በመሆንዋ ቀደምት ሀገር ያደርጋታል፡፡ በዚህም የሀገራችንን የቱሪዝም መለያ ብራንድ “ምድረ ቀደምት!” እንድንል እድል ሰጥቶናል፡፡

ይኸውም የቱሪስት ፍሰቱ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ለመምጣቱ አብነት ሊሆን የሚችል እውነታ ነው፡፡ በሆኑም በርካታ የስራ እድሎችን ስለሚፈጥር የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ቅርሶቻችንና መስህቦቻችንን በመንከባከብበ በመጠበቅና በማልማት ለጉብኝት ምቹ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ ብዙ የቤት ስራዎች ይጠበቁብናል፡፡ የቱሪስት አገልግሎት አሰጣጣችንንና የመስተንግዶ አገልግሎታችንን በማላቅ አለም ዓቀፍ ደረጃውን የጠበቀ በማድረግ ወደ አገራችን የሚመጡ ቱሪስቶች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እንዲጨምርና የቱሪስት ቆይታ ጊዜ ለማራዘም በትጋት መስራትም ያስፈልጋል፡፡

በዚህም አገራችን የምታገኘውን የውጪ ምንዛሪ ገቢ እንዲያድግና ሕብረተሰቡ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር በቀጣይ ትኩረት የሚፈልጉ ስራዎች ናቸው፡፡





ከዚህ አንጻር የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ ይህን እውን ለማድረግ የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ተቋም በዘርፉ ተፈላጊ የሆነ ብቃትና ጥራት ያለውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት፣ ተገቢውን ስልጠና በመስጠትና ለኢንዱስትሪው የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን በማሻሻል የሀገራችንን ቱሪዝም በዘላቂነት ለማልማትና ተወዳዳሪነቱን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ በዘርፉ አገልግሎት ላይ ትኩረት በማድረግ የማሰልጠኑን ተግባር በብቃት ለመወጣት ጥረት በማድረግ ላይ የሚገኝ አንጋፋ ተቋም ነው፡፡

በመሆኑም በሆቴልና ቱሪዝም የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ባለፉት ዓመታት የተመዘገቡ ውጤቶች ሀገራችን የጀመረችውን የህዳሴ ጉዞ ለማሳካት ተገቢውን ብቃት የተላበሰ የሰው ኃይል የማፍራት ተልዕኮ ለማሳካት ኢንዱስትሪ ተኮር አሰራሮችን በመዘርጋት ከመቸውም ጊዜ በላቀ መልኩ መስራት ይጠበቅበታል፡፡ ይህን ከዳር ለማድረስ በዘርፉ ከሚገኙ ባለድርሻዎችና የህዝብ ክንፎች ጋር በዕቅድ ላይ የተመሠረተ ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር ወሳኝ ነው፡፡

በዘርፉ ሙያተኞችን ማሰልጠንና ለኢንዱስትሪው የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል የመንግስት ኃላፊነት ብቻ ባለመሆኑ ባለድርሻ አካላትና መላው የህብረተሰቡ ክፍል በባለቤትነት የስልጠናውን ተደራሽነትና ጥራት ለማሳደግ እንዲሁም የዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል በብዛትና በጥራት በማፍራት የቱሪዝም ልማታችንን ለዘላቂና ሁለንተናዊ ዕድገት ለመጠቀም ሁሉም የድርሻውን መወጣት እንደሚገባ እያሳሰብኩ ለስኬታማነቱ ሚኒስቴር መ/ቤታችን ተገቢውን ድጋፍ እንደሚያደርግ ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

አመሰግናለሁ!



*“*

*ምርጥ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን ተግባራዊ በማድረግ ኢትዮጵያን ተመራጭና ተወዳዳሪ የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ ከሌሎች ተቋማት ጋር በጋራ መስራትን ይጠይቃል!”*

አቶ አሸብር ተክሌ

የሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ. ዋና ዳይሬክተር

የልማት ቁልፍ መሰረቱ በዳበረ የአሰለጣጠን ስርዓት የተካነ፣ ብቁና የተግባር ባለቤት የሆነ የሰው ሀይል ነው፡፡ አገራችንም ይህን መሰረት በማድረግ ለትምህርትና ስልጠናው ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እየሰራች ትገኛለች፡፡ ለከፍተኛ ትምህርትም ሆነ ለቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ትኩረት በመስጠት ኢኮኖሚያችን በየደረጃው የሚፈልገውን የበቃ የሰው ሀይል እየፈጠሩ ወደ ስራ ገበያው ማስገባት የወቅቱ ትኩረት ነው፡፡

የሀገራችን ልማት ኢንዲፋጠን መንግስታችን ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት በሁለተኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ውስጥ ልዩ ስፍራ እንዲኖረው በማድረግ በዚህም አገራችን የምታገኘውን የውጪ ምንዛሪ ገቢያችን እንዲያድግና ዘርፉን እንደ አንድ የስራ እድል መፍጠሪያ ዘርፍ በማድረግ ህብረተሰቡ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ምቹ ሁኔታዎች ፈጥሯል፡፡ አገራችን ቱባ የቱሪስት መስህቦች ያሏትና የበርካታ ብሔር፣ብሔረሰቦችና ህዝቦች ባህሎችና ቅርሶች መገኛ መሆኗ ይታወቃል፡፡ ከሁሉ በላይ ኢትዮጵያ፣ ምድረ-ቀደምት (Ethiopia, Land of Origins) በመሆኗ በዓለም ዓቀፍ ደረጃ በቱሪዝም ዘርፉ ልዩ ስፍራ እንድታገኝ አድርጓታል፡፡

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ተጠሪ የሆነው የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በዘርፉ ፈጣን እድገት እንዲመጣ፤ በአለም ዓቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ የሆነ ሰው ሃይል በማቅረብ፤ችግር ፈቺ ጥናትና ምርምር እንዲሁም የማማከር አገልግሎት በመስጠት ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው እድገት የራሱን አስተዋፅኦ እያደረገ የሚገኝ አንጋፋ ተቋም ነው፡፡

በአሁኑ ሰዓት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ዘርፍን ውጤታማ ለማድረግ ኢንዱስትሪው ከሙያ ደረጃ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ምዘና ባለው ሰፊ የስልጠና ሂደት ባለቤት ሆኖ የመሪነት ሚናውን ለመወጣት በቅንጅት እየሰራ ይገኛል፡፡



የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
Catering and Tourism Training Inistitute

በዚህም መነሻነት በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ሃገሪቱ ያላትን እምቅ ሃብት እንደ ሀገር በሰለጠነና በበቃ የሰው ሃይል በመምራት፣ምርጥ ቴክኖሎጂዎችንና አሰራሮችን ተግባራዊ በማድረግ ኢትዮጵያን ተመራጭና ተወዳዳሪ የቱሪስት መዳረሻ ለማድረግ ከሌሎች ተቋማትጋር በጋራ በመስራት የበኩሉን ጥረት በማድረግ ላይ ነው፡፡ይህንን ለማሳካትና ስልጠናዎችን ተደራሽ ለማድረግ ረገድ በሁሉም ክልሎች በሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻ ቦታዎች የክላስተር ማዕከላትና በሥራቸው ሳተላይት ተቋማትን በመምረጥና በማቋቋም የዘርፉን የሰው ኃይል እጥረት በአጭር ጊዜ ለመፍታት  እየሰራ ይገኛል፡፡ በተለይ የተቋም አሰልጣኞችንና ኢንዱስትሪ ባለሙያዎችን በማቀናጀት የአሰልጣኞች ስልጠና በውጭና በሀገር ውስጥ ሰፊ ልምድና ዕውቀት ባላቸው አሰልጣኞች በማሰልጠን የስልጠና ጥራት ለማሻሻል በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

የዓለም ቱሪዝም ድርጅት መረጃ እንደሚያመለክተው ዘርፉ ከአስር ሰው ለአንዱ የስራ ዕድል የመፍጠር አቅም ያለው በመሆኑ ሃገራችን ከሏት ቱባ የተፈጥሮና ባህላዊ ሃብት አንጻር ይህን በአግባቡ ለመጠቀም የሚችሉ ብቃት ያለው የሰው ሃብት ማፍራት ይጠይቃል፡፡

በመሆኑም የህዝብና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ያዘጋጀው የተቋማችንን የስራ እንቅስቃሴ በአጭሩ በምታሳየው  መጽሄት ላይ አጠቃላይ መረጃዎችን በመገንዘብ ስለተቋማችን ያላችሁን ግንዛቤ የበለጠ ታዳብሩበታላችሁ ብዬ አስባለሁ መልካም ንባብ፡፡

አመሰግናለሁ!



*“የስልጠናውን ጥራት አስተማማኝ ደረጃ ላይ ለማድረስ ተቋማችን ብቃት ባለው አመራር፣ አሠራርና አደረጃጀት እንዲመራ ለማድረግ አመራሩን አሠልጣኞችን እና ፈፃሚዎችን በአመለካከትና በክህሎት እንዲሁም ከግብዓት አቅርቦት ጋር የተያያዙ ችግሮችን መፍታት ተገቢ ይሆናል፡፡”*

አቶ ሀብተስላሴ ኪዳኔ
ም/ዋ/ዳይሬክተር

በአገራችን ባለፉት ዓመታት የታየው አበረታች የኢኮኖሚ እድገት ለውጥ የበለጠ እንዲፋጠንና የሁለተኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ እንዲሳካ ልዩ ትኩረት ከተሰጡት የኢኮኖሚያዊና የማህበራዊ መስኮቻችን እውቅና አግኝቶ የመሪነቱ ሚና ከያዙ የኢኮኖሚ ዘርፎች አንዱ የቱሪዝም ኢንዱስትሪ መሆኑ ታምኖበት በታላቅ ትኩረት እየተሰራበት ይገኛል፡፡ ሀገራችን ሰፊና ዕምቅ የቱሪዝም ሀብት ባለቤት ናት፡፡ ይህንኑ ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም ሀገራችን ከግብርና መር ኢኮኖሚ ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ የምታደርገውን ኢኮኖሚያዊ የመዋቅር ሽግግር እንዲሳካ ተቋማችን  ከተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት አንፃር በሆቴልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪ ተፈላጊ የሆነ ብቃትና ጥራት ያለውን የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት፣ ተገቢውን ስልጠና በመስጠትና የኢንዱስትሪውን የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን በማሻሻል የሀገራችንን ቱሪዝም በዘላቂነት ለማልማትና ተወዳዳሪነቱን ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ ጠንክሮ እየሠራ የሚገኝ አንጋፋ ተቋም ነው፡፡

በመሆኑም በሆቴልና ቱሪዝም የትምህርትና ስልጠና ዘርፍ ባለፉት ዓመታት ያስመዘገብናቸው ውጤቶች ሀገራችን የጀመረችውን የህዳሴ ጉዞ ለማሳካት የተጣለብንን ብቁ የሰው ኃይል የማፍራት ተልዕኮ ለማሳካት የአሰልጣኞችን ብቃት በማሳደግ፣ የስልጠና ግብአት በማሟላትና ተገልጋይ ተኮር አሰራሮችን በመዘርጋት ተቋማዊ ለውጥን ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ከመቸውም ጊዜ በላቀ መልኩ በዘርፉ ብዙ ጥረቶችን በማድረግ ላይ እንገኛለን፡፡ ተቋሙ ያስቀመጠውን ተልዕኮና ግብ የሀገራችራንን ህዳሴ ከማረጋገጥ አንፃር የበኩሉን ሚና ለመጫወት ያለው ተቋማዊ ቁርጠኝነትና ስር ነቀል ተቋማዊ ለውጥ ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት ዘርግቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡

ከዚህ ባሻገር ሰልጣኞቻችን ብቃታቸውን በሚያረጋግጥ መልኩ ተቋማዊ ምዘናና ብሔራዊ የሙያ ብቃት ምዘና በመውሰድ የስልጠናውን ጥራት ለማስጠበቅ እንዲሁም ሰልጣኙ በራሱ





የሚተማመን እንዲሆን ለማድረግ እየሰራን እንገኛለን፡፡

ይሁን እንጂ ለማሳካት ካሰብነው ራዕይ፣ ተልዕኮና ግብ አንፃር ሲታይ የስልጠናው ተደራሽነትና ጥራት በጥልቀት ፈትሸን የላቀ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚገባን መገንዘብ ተገቢ ነው፡፡ ለዚሁም ሁላችንም በየእርከናችን ያለንን ድርሻ አሟጠን በመተግበር በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ከሚገኙ ወሳኝ ባለድርሻዎችና የህዝብ ክንፎቻችን ጋር በዕቅድ ላይ የተመሠረተ እና በየጊዜው የሚገመገም ቅንጅታዊ ሥራ ማጠናከር ይጠበቅብናል፡፡

ከዚህ አኳያ የስልጠናውን ጥራት አስተማማኝ ደረጃ ላይ ለማድረስ ተቋማችን ብቃት ባለው አመራር፣ አሠራርና አደረጃጀት እንዲመራ ለማድረግ አመራሩን አሠልጣኞችን እና ፈፃሚዎችን በአመለካከትና በክህሎት እንዲሁም ከግብዓት አቅርቦት ጋር የተያያዙ ችግሮችን መፍታት ተገቢ ይሆናል፡፡ ሰልጣኞችም በመልካም ስነ-ምግባር እንዲታነፁና ዲሞክራሲያዊ ባህልን እንዲያጎለብቱ በሚያስችል መልኩ ምርጥ ተሞክሮ ያላቸውን ሃገራት ልምድ በመለየት ተሞክሯቸውን በመቀመርና በማስፋፋት እንዲሁም በስነ-ምግባር የታነፀ ሀገር ተረካቢ ዜጋ የማፍራት ሥራዎች አጠናክሮ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

በመጨረሻም በዘርፉ ሙያተኞችን ማሰልጠንና ለኢንዱስትሪው የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻል የመንግስት እና የተቋሙ ኃላፊነት ብቻ ባለመሆኑ ባለድርሻ አካላትና መላው የህብረተሰቡ ክፍል በባለቤትነት ስሜት የስልጠናውን ተደራሽነትና ጥራት ለማሳደግ እንዲሁም የዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል በብዛትና በጥራት ለማፍራት የቱሪዝም ልማታችንን ለዘላቂ ሰላምና ሁለንተናዊ ዕድገት ለማምጣት በአንድነት እንስራ እያልኩ መልዕክቴን አስተላልፋለሁ፡፡

አመሰግናለሁ !

# የተቋሙ ታሪካዊ ዳራ

በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም(UNDP) አማካኝነት እ.ኤ.አ.1964 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቱሪስት ድርጅት ተቋቋሟል፡፡ በቱሪስት ድርጅት የቱሪዝም አመራር በነበሩት አስራኤላዊ ሚስተር ደቪድ ኤፍራታ አማካኝነት ከአገራቸው መንግስት ጋር በመነጋገር የእስራኤል መንግስት ባደረገው ድጋፍ በራስ ሆቴል የመማሪያ ክፍሎች በመከራየት በሆቴል ዘርፍ ሃያ አራት ተማሪዎችን ተቀብሎ ሥልጠና እ.ኤ.አ.1969 ዓ.ም ጀመረ፡፡

በጊዜው በቱሪስት ድርጅት ውስጥ በነበሩት የሥራ ኃላፊዎች እና በእስራኤላውያን ግፊት መንግስት ለዘርፉ ዕድገት ትኩረት ሰጥቶ እስከ አሁን ማሰልጠኛ ተቋሙ የሚጠቀምበትን ህንፃ ሊገነባ ችሏል፡፡ የሚመደብለት በጀትም በወቅቱ በኢትዮጵያ ቱሪስት ድርጅት ሥር እና በንግድና ኢንዱስትሪ ሥር ነበር፡፡

የመጀመሪያው የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተር ሚስተር ዴቪድ ኤፍራታ ሆነው ሌሎች ኤክስፐርቶች በእንግዳ አቀባበል፣ በቤት አያያዝና በመስተንግዶ የአንድ ዓመት ሥልጠና በመስጠት ሲሰራ ቆይቶ በ1973 እ.ኤ.አ የስዊዝ ዜጋ የሆኑት ሚስተር ደትማን ደግሞ የምግብ ዝግጅት ስልጠና በተጨማሪነት እንዲሰጥ አደረጉ፡፡

ተቋሙ በዘርፉ ስልጠና መስጠት ሲጀምር በተወሰኑ የሙያ ዘርፎች ቢሆንም በሃገራችን እያደገ የመጣው የኢንቨስትመንት እና የነፃ ኢኮኖሚ ስርዓት በመኖሩ በሀገራችን ውስጥ የሆቴል፣ሬስቶራንት፣ ሎጅ፣መዝናኛዎች በአስጐብኚ ድርጅቶች የሰለጠነ የሰው ኃይል ፍላጐት እያደገ በመምጣቱ ተቋሙ ስልጠናውን በስፋት አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡





# ዋና ዋና የማሰልጠኛ ተቋሙ የስራ እንቅስቃሴ

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ላለፉት 49 ዓመታት በዘርፉ የሚፈለገውን የሰለጠነ የሰው ሀይል በማቅረብ ለሀገራችን የሆቴልና ቱሪዝም ኢንዱስትሪ እድገት የላቀ አስተዋጽኦ እያበረከተ የሚገኝ ፈርቀዳጅ ተቋም ነው፡፡

ኢንስቲትዩቱ በመማር ማስተማር የኢንዱስትሪውን አብይ ዓላማ ለማሳካት በተያዘው ዕቅድ በሀገራችን ጥራቱን የጠበቀ ስልጠና፣ጥናትና ምርምር እንዲሁም የማማከር አገልግሎት ለበርካታ ዓመታት ሲሰጥ ቆይቷል፡፡

በመሆኑም እያደገ የመጣውን የሆቴልና ቱሪስት እንቅስቃሴ በሰለጠነ የሰው ሃይል ለመምራት በመደበኛ፣በማታና በአጫጭር ስልጠና መርሐ-ግብሮች የኢንስቲትዩቱን ስትራቴጂክ ዕቅድ በማዘጋጀት ርብርብ እየተደረገ ይገኛል፡፡

ተቋሙ ለቀጣይ አስር ዓመታት ማለትም ከ2008 አስከ 2017 ዓ.ም የጉዞ አቅጣጫን የሚያሳይ ፍኖተ ካርታ በማዘጋጀት ወደ ስራ ገብቷል፡፡ በፍኖተ ካርታው ላይ የተቀመጡትን ስትራቴጂዎችን በመጠቀም ኢንስቲትዩቱ በቀጣይ በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ ሙያተኞችን በማሰልጠን በ2007/8 በተጠናው ጥናት መሰረት በስራ ላይ ያለውን 23%ወደ 80% ለማድረስ ከዩኒቨርሲቲዎችና ከክልሎች ጋር በመተሳሰር ስልጠናዎችንና የሙያ እገዛ በመስጠት ኢንዱስትሪው ላይ ያሉትን ሙያተኞች ማብቃት፣ የጥናትና ምርምር ስራዎችን ማድረግና የቴክኖሎጂ ሽግግር ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡

## የስልጠና ተደራሽነትን ማስፋፋትና የአገልግሎት ጥራትን ማሻሻል

ከክልል ባህልና ቱሪዝም ቢሮዎችና ቴክኒክና ሙያ ተቋማት ጋር አስራ አንድ የክላስተር ተቋማት እና ሌሎች ሳተላይት ተቋማት እንዲቋቋሙና ኢንዱስትሪው የሚፈልገውን ሁሉ ለማሟላት 2009 ዓ.ም በተዘጋጀው የጋራ

ዕቅድ ላይ በመመስረት ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በዚህም ከክላስተር ማዕከላት ጋር በመሆን ያሰልጣኞች ስልጠና በተለያዩ ጊዜያት ተሰጥቷል፡፡

የኢንስቲትዩቱ የ2010 የ9 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም እንደሚያመለክተው በሃገር አቀፍ ደረጃ ለማሰልጠን የታቀደው የምግብ ዝግጅት ባለሙያዎችና በምግብ ዝግጅት ዘርፍ ላይ ስልጠና ለሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ተቋማት አሰልጣኞች የተሻለ እውቀትን የሚያስጨብጥ በተግባር የተደገፈ የአጭር ጊዜ የአስልጠኞች ስልጠና ዓለም ዓቀፍ ልምድ ባላቸው የምግብ ዝግጅት ባለሙያዎች የመጀመሪያ ዙር በታህሳስ ወር 2010 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳድር ተጀምሯል፡፡

ስልጠናው የኢንዱስትሪ ባለሙያዎችና አሰልጣኞችን በአንድ ላይ በመስጠት የመምህራንን አቅም የገነባ ሲሆን በሆቴል ዘርፍ የሚሰጠውን ሥልጠና ጥራት በማረጋጥና ብቃት ያለው ሰልጣኝ ለኢንዱስቲሪው ለማቅረብ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡

እንዲሁም በሆቴልና በተቋማት ያሉ አሠልጣኞችን በማቀናጀት የጋራ ግንዛቤና ክህሎትን በማሳደግ ለኢንስቲትዩቱ ሰልጣኞች በየሆቴሎች የሚሰጠውን የትብብር ሥልጠና ውጤታማ በማድረግ እና በሆቴሎች የሚሠጠውን አገልግሎት ጥራት ለማሳደግ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡

በክልል ተቋማት ጥያቄ ላይ በመመስረት የሚሰጡ አጫጭር ስልጠናዎች በቱሪዝም፣ በእንግዳ አያያዝና ሆቴል አገልግሎት፤ የምግብና መጠጥ መስተንግዶ ሙያተኞችን በቤኒሻንጉል ጉምዝ ፣ ደቡብ ብ/ብ/ሕዝቦች ፣ አፋር ፣ ድሬደዋና፣ አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ለ1291 ባለሙያዎች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም በአጫጭር ስልጠናዎች ለ2200 ሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ተቋሙ ሰልጣኞቹን ለመቀበል በሀሉም ክልሎች ላይ ምልመላ በማካሄድ በ2010 ዓ.ም 720 አዲስ ገቢ ሰልጣኞችንና 1323 ነባር ሰልጣኞችን በመቀበል በጠቅላለው 2043 ሰልጣኞች በትምህርት ላይ ይገኛሉ፡፡







## የጥናትና ማማከር አገልግሎት

የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሀገራዊ የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የሰለጠነ የሰው ሀይል የኢንዱስትሪውን ፍላጎት ጥናት ያከናውናል፡፡ በ2008 በሀገር ደረጃ ያለው ሀገራዊ የሰለጠነ የሰው ሃይል ብዛትና የኢንዱስትሪው ፍላጎት ጥናት ተደርጎ በኢንዱስትሪው ላይ ያሉ ችግሮችና የመፍትሔ አቅጣጫ ተለይተው እየተሰራበት ነው፡፡ በተጨማሪም በ2010 ዓ.ም በሀገር አቅፍ ደረጃ በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ የተሰማራውን በሙያው የሰለጠነ የሰው ሀይል ከኢንዱስቲሪው ፍላጎት አንጻር በምን ደረጃ እንዳለና የሚያያፈልገው የስልጠና አይነት ለይቶ በማወቅ በቀጣይ ስራውን የመፍትሄ ስትራቴጂ የሚያስቀምጥ ጥናት ተጠንቷል፡፡

የ2010 የተቋሙ መረጃ እንደሚያሳየው 36 የኢንስቲትዩቱ መምህራን በትምህርት ክፍላቸው የማማከር አግልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

ተቋሙ በሚያደርገው የስልጠና ጥራትን ለማሻሻልና ለማስፋፋትከሀገር ውስጥ አቻ ተቋማትና ውጭ አለለምዓቀፍ ድርጅቶች ጋር ግንኙነቶችን በመፍጠር የተለያዩ የመግባቢያ ሰነዶችን ተፈራርሟል፡፡ ለአብነት ያህል ከሀገር ውስጥ የሲቪል አቪዬሽን አካዳሚ፣ የፌዴራል ቴ/ሙ/ት/ስልጠና ኤጀንሲ፣ የአዲስ አበባ ሆቴል ባለቤቶች ማህበር፣ የኢትዮጵያ ምግብ ዝግጅት ባለሙያዎች ማህበር እና ሌሎቹም ሲሆን ከዓለም ዓቀፍ ድርጅቶች ውስጥ ደግሞ የዓለም ቱሪዝም ድርጅት(UNWTO) እና የካናዳ ኮሌጅ ኦፍ ዘ ሮኪስ(Canada College of the Rockies)ይገኙበታል፡፡

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከአስር ዓመታት በላይ የዓለም ቱሪዝም ድርጅት(UNWTO) አባል ሆኖ የቆየ ሰሆን በ2009 እና 2010 በተደረገው ጠንካራ የግንኙነት ስራዎች ዋና ጸሀፊው ዶ/ር ታሌብ ራፋይ ተቋሙን በጎበኙበት ወቅት ባደረጉት ንግግር በየዓመቱ አምስት የተቋሙ ሰልጣኞችን ድርጅታቸው ተቀብሎ ስልጠና እንደሚሰጥ ቃል ገብቷል፡፡ ይህን ተከትሎ ነው የመግባቢያ ሰነዱ(Memorundum Of Understanding) የተፈረመው፡፡










የተቋሙ የ2010 የ9 ወራት ዕቅድ ክንውን እንደሚያሳየው ይህን ተግባር ለማሳካት የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎችና የድርጊት መርሃ-ግብር በመዘጋጀት ላይ ይገኛል፡፡

ከካናዳ ሮኪስ ኮሌጅ ጋር በተደረገው ስምምነት (Memorundum of Understanding) ሁለት ባለሙያዎች በካናዳ መንግስት ሙሉ ወጪ ወደ ኢትዮጵያ በመምጣት በቱሪዝም ዘርፉ ላይ ከኢንዱስቲሪው እንዴት በመቀናጀት መሥራት እንደሚቻል ከኮሌጁ ጋር በጋራ ሥልጠና መስጠት በሚቻልበትን ሁኔታ በማጥናት በቀጣይ ኢንስቲትዩቱ ወደ ተሻለ አፈጻጸም የሚያድግበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡



## የትብብር ስልጠናዎችና የሰልጣኞች የተግባር ስልጠና

### የትብብር ስልጠና

በሀገራችን ተግባራዊ እየሆነ ያለው የትብብር ስልጠና የሁለትዮሽ ስልጠና ስርዓት(dual training system)ነው፡፡ መሰረተ ሃሳቡም በኢንዱስትሪዎችና በቴ/ሙ/ት/ሥ ተቋማት ትብብር አስቀድሞ በሚዘጋጅ እቅድ መሰረት የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠናን ሰልጣኞች በሆቴሎችና በቱሪስት አስጎብኚ ድርቶች ውስጥ በትምህርት ያገኙትን እውቀት ተግባራዊ

የማያደርጉበት ነው፡፡ በዚህ ስርዓት ውስጥ ኢንዱስትሪዎቹ እና የቴ/ሙ/ት/ሥ ተቋማቱ ሰልጣኙ ወደ ስራው ዓለም ሲሰማራ የተሻለ የመፈፀም ብቃት እንዲኖረው የሚያስችል ስልጠና እንዲያገኝ የማድረግ ኃላፊነቱን በጋራ የሚወስዱ ሲሆን ኢንዱስትሪዎቹ የተግባር ስልጠና ቦታዎችን ሲያዘጋጁ የቴ/ሙ/ት/ሥ ተቋማቱ ደግሞ አጠቃላይ፣ልዩ እና ሙያ ነክ የንድፈ ሃሳብ ትምህርቶችን ይሰጣሉ፡፡



በሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት የሚገኙ ሰልጣኞች በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ላይ ተሰማርተው ከሚገኙ ድርጅቶች ጋር ተቋሙ ባደረገው ስምምነት መሰረት 30 በመቶ የስልጠና መርሐ ግብሩን ወይም የጽንሰ ሀሳብ ስልጠናን ከወሰዱ በኋላ ከኢንዱስትሪው ጋር በመሆን 70በመቶ በተግባር እንዱስትሪው ላይ በመሄድ ስልጠናቸውን ያጠናቅቃሉ፡፡

በትብብር ስልጠናው ለሰልጣኞች የስልጠና ቦታ ማዘጋጀት የሚችል እና ተገቢውን የሙያ ብቃት ምዘና በአጥጋቢ ሁኔታ ያለፈ ሰልጣኝ ወደ ድርጅቶቹ ሄዶ ቀሪውን የተግባር ስልጠና ይከታተላል፡፡





## የትብብር ስልጠናው ለተሳታፊዎች የሚያስገኘው ፋይዳ

### ሀ. ለድርጅቶች

ድርጅቶቹ የስራ መስካቸው የሚጠይቀውን ዓይነት ብቃት ያለው የሰው ሃይል ለማፍራት በሂደቱ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ መሆን ይችላሉ፣ ድርጅቶቹ የተሻለ ብቃት ያለውን ሰራተኛ በቀላሉ ለመመልመልና ለመምረጥ እንዲችሉ መልካም አጋጣሚን ይፈጥርላቸዋል፣ እንዲሁም በመምህራንና በሰልጣኞች አማካኝነት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ከትምህርትና ስልጠና ተቋማት ወደየድርጅቶቻቸው በቀላሉ ማሸጋገር ይችላሉ፡፡

ድርጅቶቹ በበኩላቸው ካለባቸው ሃገራዊና ማህበራዊ ሃላፊነት አኳያ ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክቱ ያስችላቸዋል፣ በትብብር ስልጠናው ሂደት ወቅት እንደ አስፈላጊነቱ ተጨማሪ ስልጠና እንዲካሄድና የትብብር ስልጠናውን አስመልክቶ ሀሳብ ማቅረብ ይችላሉ፡፡

### ለ. ለሠልጣኞች

በእውነተኛው የስራ ዓለም ላይ ተሰማርተው እንዲሰሩ እና የስራውን ዓለም ነባራዊ እውነታ እንዲያውቁ እድል ይፈጥርላቸዋል፣ከስልጠናው በኋላ ሊቀጥራቸው በሚችል ድርጅት ውስጥ ስለሚሰሩ ለተቀጣሪነት ብቁ ሆነው ለመገኘት እንዲጣጣሩ ይገፋፋቸዋል፡፡

የስልጠናው ሂደት ከተቋሙ ባገኙት የንድፈ ሃሳብ እውቀት ላይ ተግባራዊ ችሎታዎችን በማከል ብቃታቸውን እንዲያጎለብቱ የሚረዳቸው ሲሆን፣ ከመመረቃቸው አስቀድሞ ስራ ላይ መሰማራት፣ መቻላቸው እርካታን ይፈጥርላቸዋል፡፡ አንድ ሰራተኛ ውጤታማ እንዲሆን ከተፈለገ የማሰላሰልና በጥልቀት የማሰብ ችሎታውን መጠቀም እንዳለበት ያስገነዝባቸዋል፡፡

ይህ ኢንዱስትሪው ብዙ የተማረ የሰው ኃይል የሚፈልግ በመሆኑ ስልጠና በተከታተለበት ድርጅት ስራን ለማገኘት ሰፊ እድል አለው፡፡



## ሐ. ለተቋሙ

የተግባር ስልጠናው በኢንዱስትሪ ውስጥ የሚካሄድ እንደ መሆኑ ለተቋማችን የስልጠና መሳሪያዎችንና ሌሎች ለስልጠናው የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ለመግዛት ወጪ ከማዉጣት ይልቅ ወጪን እንዲቆጥብ ያስችላል፡ ፡ በተጨማሪም መምህራኑ ከነባራዊው የስራ ዓለም ጋር እንዲተዋወቁ ያስችላቸዋል፣በሆቴሎችና ቱሪስት አስጎብኚ ድርጅቶች ጋር የሚካሄደው የትብብር ስልጠና የተቋማችንን የምሩቃን ተፈላጊነት አስመልክቶ ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ በውል ለመረዳት ዕድል ይፈጥራል፡፡

በሌላ በኩልም ተግባራዊ ስልጠና የሚሰጠው ተገቢውን የቴክኖሎጂ መሳሪያዎችን በመጠቀም መሆኑን ለማረጋገጥ ያስችለዋል፣ በትብብር ስልጠና ወቅትም ብቃት ያላቸውን ሰልጣኞች በተግባር በመፈተን በቀጣይ ከምርቃት በኋላ የስራ እድልን ይፈጥርላቸዋል፡፡





## ትምህርታዊ የጉብኝት መርሃግብር

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከትብብር ስልጠና ውጭ ትምህርታዊ የጉብኝት መርሐ-ግብሮችን በማዘጋጀት የሰልጣኞችን እውቀት እንዲዳብር ያደርጋል፡፡ ትምህርታዊ ጉብኝት ሰልጣኞች በክፍል ውስጥ የሚማሩትን የትምህርት አይነት መሰረት በማድረግ በተግባር ቦታው ድረስ በመሄድ የሚመለከቱበት መርሃ-ግብር ነው፡፡ ይህም ኢንስቲትዩቱ በቱሪዝም ዘርፍ ሰልጣኞች በንድፈሀሳብ የተማሩትን በአካል በመጎብኘት ነባራዊ ሁኔታውን እንዲገነዘቡት ያደርጋል፡፡ በዚህም በሀገራችን የሚገኙ የቱሪስት መስህብ ቦታዎች በሙሉ በሚዘጋጀው መርሐ-ግብር መሰረት ይጎበኛሉ፡፡





# በተቋሙ የሚሰጡ መርሐ-ግብሮች (ስልጠናዎች)

በተቋሙ ውስጥ ኢንግሊዘኛ፣ፈረንሳይኛና ጀርመንኛ፣ ሳይኮሎጂ፣ IT፣እንተርፕሪነርሺፕ እና የመጀመሪያ እርዳታ (Frist aid) የስልጠና መስኮች ያሉ ሲሆን በሰልጣኞች ጥያቄ መሰረት የአጫጭርና የሥራ ላይ ሥልጠናዎችንም ይሰጣሉ፡፡

| Sn | Occupational Level | Occupational Title/ Department |
|---|---|---|
| 1 | Degree | Vocational degree in Hotel Management |
| | | Vocational degree in Tourism Management |
| 1 | Level 5 | |
| | 1.1 | Level 5 Hotel Management |
| | 1.2 | Level 5 Tourism Management |
| 2 | Level 4 | |
| | 2.1 | Level 4 Tour Operation Supervision |
| | 2.2 | Level 4 Food and Beverage Service Supervision |
| | 2.3 | Level 4 Front Office supervision |
| 3 | Level 3 | |
| | 3.1 | Level 3 Tour Guide Service |
| | 3.2 | Level 3 Font office Operation |
| | 3.3 | Level 3 Food and Beverage Service |
| | 3.4 | Level 3 Housekeeping Service |
| | 3.5 | Level 3 Foreign Dish Cooking |
| | 3.6 | Level 3 Food and Beverage Control |
| | 3.7 | Level 3 Pastry and Bakery |
| | 3.8 | Level 3 Carting Operation |

ተቋሙ ከ1961 ዓ.ም ጀምሮ ያሰለጠናቸው ተማሪዎች አሃዛዊ መረጃ የተመራቂ ሰልጣኞች ቁጥር ከ1961 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2010 ፡-16053 ይህ መረጃ በመደበኛው መርሃግብር ሲያሰለጥናቸው የነበሩ ሰልጣኞች ቁጥርን ብቻ ያካተተ ነው፡፡





| ተ.ቁ | ዓ.ም | የሰልጣኞች ቁጥር | ተ.ቁ | ዓ.ም | የሰልጣኞች ቁጥር |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | 1961 | 24 | 26. | 1986 | 240 |
| 2. | 1962 | 44 | 27. | 1987 | 145 |
| 3. | 1963 | 13 | 28. | 1988 | 135 |
| 4. | 1964 | 18 | 29. | 1989 | 156 |
| 5. | 1965 | 23 | 30 | 1990 | 137 |
| 6. | 1966 | 54 | 31 | 1991 | 122 |
| 7. | 1967 | 73 | 32 | 1992 | 177 |
| 8. | 1968 | 80 | 33 | 1993 | 196 |
| 9. | 1969 | 14 | 34 | 1994 | 331 |
| 10. | 1970 | 13 | 35 | 1995 | 423 |
| 11. | 1971 | 21 | 36 | 1996 | 540 |
| 12. | 1972 | 55 | 37 | 1997 | 617 |
| 13. | 1973 | 70 | 38 | 1998 | 550 |
| 14. | 1974 | 65 | 39 | 1999 | 554 |
| 15. | 1975 | 64 | 40 | 2000 | 352 |
| 16. | 1976 | 38 | 41 | 2001 | 298 |
| 17. | 1977 | 96 | 42 | 2002 | 374 |
| 18. | 1978 | 58 | 43 | 2003 | 584 |
| 19. | 1979 | 69 | 44 | 2004 | 656 |
| 20. | 1980 | 92 | 45 | 2005 | 693 |
| 21. | 1981 | 75 | 46 | 2006 | 758 |
| 22. | 1982 | 88 | 47 | 2007 | 821 |
| 23. | 1983 | 47 | 48 | 2008 | 1239 |
| 24. | 1984 | 122 | 49 | 2009 | 2493 |
| 25. | 1985 | 103 | 50 | 2010 | 2043 |

ምንጭ፡ የተቋሙ ሬጅስትራር

# የቱሪዝም እድገታችን ለሰልጣኞቻችን የሥራ ዕድል ፈጠራ!

በዓለም አቀፍ ደረጃ ቱሪዝም የተሻለ አቅጣጫና አመራር አግኝቶ እንዲሁም እንደ የሥራ ዘርፍነት መታወቅ የጀመረው ከ1950ዎቹ ጀምሮ እንደሆነ በርካታ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ የ1950ዎቹ ዓመታት የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ፍፃሜ ማብቂያ በመሆኑ የዓለም ሰላም የሠፈነበትና በርካታ አገራት መልሶ የመገንባት ሂደት ውጤታማ እየሆነ የመጣበት፣ የሰዎች የገቢ ዕድገት የጨመረበት ወቅት ስለነበር የዓለም ቱሪዝም ዕድገት ለውጥ በማሳየት በርካቶች ከአገር አገር እንዲጓዙ አድርጓል፡፡

በርካታ አገራትም ዘርፉን እንደዋና የገቢ ምንጭ መጠቀም በመጀመራቸው እድገቱ እጅግ ፈጣን እየሆነ በመምጣቱ እንደ ዓለም አቀፉ የቱሪዝም ድርጅት በአሁኑ ሰዓት የዓለም ዓመታዊ የቱሪስት ፍሰት ከ 1 ቢሊየን በላይ ሆኗል፡፡ ከእነዚህ ከ 1 ቢሊየን በላይ ከሚሆኑ ተጓዦች የሚገኘው ገቢ በትሪሊየን ዶላር ሲሆን ይህም ዘርፉ ለአገራት የኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያደረገ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያም የቱሪዝምን ታሪክ ስንመለከት ዘርፉ በመንግሥት ደረጃ እውቅና የተሰጠው ከዓለም የዘመናዊ ቱሪዝም ተሞክሮ አንጻር ብዙም ሳይዘገይ እንደነበር ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ በ1950ዎቹ የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት ቱሪዝም ለአገራት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ልማት ያለውን ፋይዳ በመገንዘብ አገራችን የቱሪዝምን እንቅስቃሴ እንዲጀመር ሆኗል፡፡

ኢትዮጵያም በርካታ ታሪካዊ፣ ተፈጥሯዊና ባህላዊ ቅርሶችና መስህቦች ያሏት መሆኗን በመገንዘብ እ.ኤ.አ በ1958 የመጀመሪያውን የቱሪዝም ልማት ፕላን በማዘጋጀት በ1961 ለመጀመሪያ ጊዜ ቱሪዝምን የሚቀይስ፣ የሚያስፋፋና የሚመራ አንድ የቱሪስት ቢሮ በወቅቱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የበላይ ተቆጣጣሪነት እንዲከፈት ተደርጎ እንደነበር የተለያዩ መዛግብት ያስረዳሉ፡፡





ዛሬ የኢትዮጵያ መንግስት የቱሪዝም ዘርፉን በተሻለ አደረጃጀት በማዋቀርና ባለድርሻ አካላትን ያካተተ ፖሊሲ በማዘጋጀት መሠረታዊ ለውጦችን በማድረግና የቱሪዝም ዘርፍ የአገሪቱን መስህቦች በተሻለ ደረጃ በማልማት የሕዝቦችን የጋራ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ በርካታ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል፡፡ በዚህ መሰረት በአዋጅ ቁጥር 471/98 የፌደራል መንግሥት አስፈፃሚ አካላት አወቃቀር መሠረት “የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር” በሚኒስቴር መስሪያ ቤት ደረጃ የተቀናጁ ስራዎችን እያከናወነ ይገኛል፡፡

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱም የቱሪዝም ልማት ፖሊሲና ስትራቴጂ በማዘጋጀት ዘርፉንና የቱሪዝም መስህቦችንና ምርቶችን ለማልማተ የመሰረተ ልማት አውታሮችና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡ ይህም አገራችንን በዓለም አቀፉ የቱሪዝም ገበያ ፉክክር ውስጥ ብቁ ተወዳዳሪ እንድትሆንና የሕዝቦችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ እንደሚረዳ ይታመናል፡፡

በአገራችን ላለፉት አራት አመታት “የኢትዮጵያ ቱሪዝም ድርጅት” እና “የኢትዮጵያ ቱሪዝም ትራንስፎርሜሽን ም/ቤት” በደንብ ቁጥር 294/2005 መሠረት ተቋቁመው ስራዎች እየተሰሩ ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ትራስፎርሜሽን ምክር ቤትም በማቋቋሚያ አዋጁ ላይ በግልጽ እንደተቀመጠው በአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ሰብሳቢነት የሚመራና የሁሉንም ክልል ፕሬዝዳንቶችና የከተማ አስተዳደር ከንቲባዎችን፣ የኢትዮጵያ አየር መንገድ፣ የሆቴሎች፣ የአስጎብኚ ድርጅቶችና የሌሎች የዘርፍ ማህበራት ፕሬዝዳንቶችን፣ እንዲሁም የሃይማኖት ተቋማት መሪዎችን በአባልነት ያቀፈ ነው፡፡

ምክር ቤቱም በዋናነት በአገሪቱ የሚካሄዱ የቱሪስት መዳረሻዎችን ልማትና የማርኬቲንግ ሥራዎችን አቅጣጫ በበላይነት ይመራል፤ የቱሪዝም ዘርፉን እድገት የሚገቱ ማነቆዎችንና ቁልፍ ችግሮችን ለመፍታት ተገቢውን አቅጣጫ በመስጠትና ክትትል በማድረግ ተፈጻሚነታቸውን ያረጋግጣል፤ ለቱሪዝም ልማትና ማርኬቲንግ ሥራዎች ስኬታማነት የተለያዩ ተቋማት ድጋፍና

ቅንጅታዊ አሠራር እንዲኖር አስፈላጊውን መመሪያ ይሰጣል፤ በአጠቃላይ የአገራችን የቱሪዝም ዘርፍ ልክ እንደሌሎች ዘርፎች ሁሉ በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ላይ ሲሆን በተለይም የእንግሊዝኛ መጠሪያ የሆውን “Ethiopia, Land of Origins” አዲስ ብራንድ የአማርኛ ቋንቋ አቻ ትርጉም ምድረ ቀደምት በሚለው አገራችን በዓለም አገራት በመገኘት ማስተዋወቃችን ወደፊት ለሰነቅነው ራእይ ስኬት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡

የቱሪዝም ዘርፉን በተሻለ ሁኔታ ለማሳደግ በተለይም ከክቡር ከጠቅላይ ሚኒስትሩ ጀምሮ የየክልል ፕሬዝዳንቶችና ሌሎች የአገራችን ወሳኝ ማህበራትና ተቋማት መሪዎች የምክር ቤቱ አካል መሆናቸው ዘርፉ ያለምን ጥርጥር ተለውጦ ለሕዳሴያችን ስኬት ታላቅ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክት በማመን የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት በዘርፉ እያሰለጠናቸው ያሉ ሰልጣኞች ሰፊ የስራ እድል እንደሚኖራቸው ከፍተኛ ተስፋ ያሰነቀ ስለሆነ እንደ ስልጠና ተቋም የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ብዙ ስራዎች እንደሚጠበቁ መዘንጋት የለብንም፡፡

## ተማሪዎች ምን ይላሉ



የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ሰልጣኞች የኢንዱስትሪውን ገፀ-ባህሪ ተላብሰው ብቁና ኢንዱስትሪውን ሊመሩ የሚችሉ ሰልጣኞች እንዲሆኑ ለማድረግ በተቀመጠው የሙያ ደረጃ መሰረት የንድፈ - ሃሳብና የተግባር ስልጠናውን በማስተሳሰር ስልጠናዎች ይሰጣሉ፡፡

ሰልጣኞች በንድፈ ሀሳብና በተግባር የተደገፈ ስልጠና ከወሰዱ በኋላ





በተቀመጠው የሙያ ደረጃ (standard) መሰረት የሙያ ብቃት ምዘና ይወስዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በየዓመቱ የሚከበረው የቱሪዝምና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት ሁነት (Tourism and Hospitality week) መኖሩ በሰልጣኞች ላይ ትልቅ የራስ መተማመንና የእችላለሁ መንፈስን ይፈጥራል፡፡

ልላው በየዓመቱ የሚካሄደው የቱሪስት መስህብ ቦታዎች ጉብኝት ሰልጣኞች የቱሪስት መዳረሻ ቦታዎች ይጎበኛሉ፣ ይህ ደግሞ ሰልጣኞች ወደ ስራ አለም ሲገቡ አዲስ እንዳይሆንባቸው ትልቅ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡

በተቋሙ ለስልጠና ጥራት እየተሰጠ ያለው ትኩረት አበረታች ቢሆንም አሁንም ከኢንዱስትሪዎች ጋር ጠንካራ ግንኙነቶችን በመፍጠር፣ ለመማር ማስተማር ሂደት አስፈላጊ የሆኑ የተማሪዎች መኝታ፣ የምግብ፣ የጤና፣ ምቹ የማንበቢያ ቤተመጽሃፍት፣ የተማሪዎች ሙያዊ ልምምድ የሚያደርጉበት ስታር ሆቴል፣ የስፖርት ማዘውተሪያ የመሳሰሉትን በሚገባ አሟልቶ ስልጠና ቢሰጥ ኢንዱስትሪው ከተቋሙ የሚፈልገውን ጥራት ያለው የሰው ሃይል ያገኛል አላለሁ፡፡

የተማሪዎች ፕሬዚዳንት

ግዛቸው ክንዱ



# NEWS

**Presentation and Discussion was held with Dusit International Education in Bangkok. CTTI Public Relation (August 31, 2017)**



Catering and Tourism Training Institute (CTTI) and Dusit International Education officials had met and discussed about the relationship between the two institutions at Bangkok.

During the discussion, Dusit was represented by the President, the Dean and the Foreign Relationship Head. CTTI also represented by the General Director and the Deputy.

Dean of the International Education, had presented the activities of the Dusit International Education and about Dusit International Hotel. The historical backgrounds, objectives, duties and responsibilities of CTTI and the current situation of

the Ethiopian Hotel and Tourism Industry development was also presented by the Public and International Relation Director.



An agreement was done between both institutions to share experiences, new technology transfer, and conducting valuable researches in the hotel and tourism industry.

Lastly, Dusit International Education management members had also expressed their willing to come, share experiences and make additional visit at CTTI and the country's tourism development in the future.



የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
Catering and Tourism Training Inisitute

## ለምግብ ዝግጅት ባለሙያዎችና ለዘርፉ መምህራን የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና ተሰጠ።

**(ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ 04/05/2010 ዓ.ም)**



የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ከአዲስ አበባ መስተዳድር ባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና ከቴክኒክና ሙያ ቢሮ ጋር በመሆን በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ከአንድ እስከ ሶስት ኮከብ ደረጃ ባላቸው ሆቴሎች ውስጥ በዋና ሼፍነት ለሚያገለግሉ እና በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ውስጥ በምግብ ዝግጅት አሰልጣኝ ለሆኑት ከኢትዮጵያ የምግብ ዝግጅት ባለሙያዎች ማህበር በተመረጡ ዋና እና ዓለም ዓቀፍ ልምድ ባላቸው ሼፎች የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

የኢንስቲትዩቱ ዋና ዳይሬክተር አቶ አሸብር ተክሌ ጥር 04/2010 ዓ.ም ለጋዜጠኞች መግለጫ በሰጡበት ወቅት እንደገለጹት የእንዱስትሪውን ባለሙያዎችና አሰልጣኞችን በአንድ ቦታ በማሰልጠን ጥሩ ተሞክሮዎችን እንዲለዋወጡ ማድረግ ለዘርፉ ዕድገት ወሳኝ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ሥልጠናው የመምህራንን አቅም በመገንባት በሆቴል ዘርፍ የሚሰጠውን ሥልጠና ጥራት ማረጋጥና ብቃት ያለው ሰልጣኝ ለኢንዱስቲሪው ማቅረብ፣ በሆቴልና በተቋማት ያሉ አሠልጣኞችን በማቀናጀት የጋራ ግንዛቤና ክህሎት በመፍጠር ለኢንስቲትዩቱ ሰልጣኞች በየሆቴሎች የሚሰጠውን የትብብር ሥልጠና ውጤታማ ማድረግ እና በሆቴሎች የሚሠጠውን አገልግሎት ጥራት ማሳደግን አላማ ያደረገ መሆኑን ዋና ዳደሬክተሩ አብራርተዋል፡፡

የመጀመሪያው ዙር ስልጠና ከታህሳስ 26/2010 ጀምሮ ለአስራ ስድስት ቀናት የቆየ ሲሆን በሁሉም ክልሎች ላይ ተመሳሳይ ስልጠናዎችን ለመስጠት መታቀዱም ተገልጿል፡፡

**ስልጣኞችም በበኩላቸው እየተሰጠ ያለው ስልጠና ሙያቸውን ለማዳበር በጣም አስፈላጊ መሆኑን ገልጸዋል፡፡**

# የእንግዶች አምድ

## ‹‹በቱሪዝም ልማት ለመሳተፍ በቂ ግንዛቤና ስልጠና ኖሮት የሃብቱ ተጠቃሚ የሚሆን ማህበረሰብ ማፍራት አለብን››

ዶ/ር ሙሉጌታ ፍስሃ



ዶ/ር ሙሉጌታ ፍስሃ ይባላሉ አብዛኛውን ጊዜያቸውን በቱሪዝም ዘርፍ ጥናትና ምርምር ያደረጉ ባለሙያ ናቸው፤በአሁኑ ገዜም በአዲስ አበባ ዩንቨርሲተቲ በመምህርነት እያገለገሉ ይገኛሉ በዚህ ልዩ መጽሄታችን ስለ ስራቸው ጥቂት ሊያካፍሉን እንግዳ አድርገናቸዋል መልካም ንባብ ፡፡

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ፡- ከሁሉ አስቀድሜ ለዚህ ቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ሆነው ጊዜውን ስለሰጡን ከልብ እያመሰገንኩ ራስዎን ያስተዋውቁን

ዶ/ር ሙሉጌታ፡- ዶ/ር ሙሉጌታ ፍስሃ እባላለሁ በአ.አ.ዩ የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር ነኝ

እንዲሁም በተፈጥሮ ሳይንስ ኮሌጅ አስተማሪም ተመራማሪም ነኝ፡፡ ከዚህ ባሻገር ላለፉት 14 ዓመታት ምርምር በማድረግ ከጓደኞቼ ጋር በመሆን ስድስት መጽሃፍትን በእንግሊዝኛና በአገርኛ ቋንቋ አሳትመናል፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ ቱሪዝም ላይ የምንችለውን ሁሉ እያበረከትን ነው፡፡

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ፡- የታተሙት መጽሃፍት ስድስቱም ስለቱሪዝም የሚያወሩ ናቸው?

ዶ/ር ሙሉጌታ፡- አዎ ሁሉም ስለቱሪዝም የተፃፉ ናቸው፤ ገና አልታተመም





እንጂ ሰባተኛውንም አዘጋጅተነዋል፡፡

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ፡- መጽሃፍቱንና በዋናነት የያዙትን መልእክት ዘርዘር አድርገን ብናያቸው?

ዶ/ር ሙሉጌታ፡- መልካም Fundamentals of Transforming the Ethiopian Truism Industry ይላል፡፡ የአማርኛው ደግሞ የኢትዮጵያ ሃብትና የቱሪዝም ልማት የሚል የመጨረሻው ተመሳሳይ የሆነ ሃሳብ ያለው ሆኖ በትግሪኛ ነው፡፡ ሌሎቹ ሁለት ጥናታዊ የሆኑት መጽሃፍት ደግሞ አንደኛው በአድዋ ቱሪዝም እና በደብረታቦር ላይ ያተኮረ ሲሆን በሁለቱ መጽሃፍት ሊተላለፍ የተፈለገው መልእክት ያለንን የቱሪዝም ሃብት መጠቀም እንደሚገባንና ማህበረሰባችን በቱሪዝም ልማት ለመሳተፍ ዝግጁ አይደለም የሚል ነው፡፡ ዝግጁ ያልሆነው ደግሞ ከትምህርት እጥረት በመሆኑ በቱሪዝም ልማት ለመሳተፍ በቂ ግንዛቤና ስልጠና ኖሮት የሃብቱ ተጠቃሚ የሚሆን ማህበረሰብ ማፍራት አለብን የሚል መልዕክትን ያስተላልፋል፡፡

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ፡- እንዴት ወደ ሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ማህበረሰብ ሊቀላቀሉ እንደቻሉ ቢያስረዱኝ፤

ዶ/ር ሙልጌታ፡- ብዙ የሙያ መስኮች የሚታይበት ስለሆነ ተቋሙን በተለያዩ ነገሮች በማገልገሌ በገንዘብ የማይተመነውን የደስታ ምንጭ ይሰጠኛል፡፡ እንዴት ለሚለው ጥያቄ ለመመለስ የኢትዮጵያ የቱሪዝም ሃብቶችን ወደ ልማት መቀየር ስንል አንድ የልማት ውጤት ሆስፑታሊቲ እንዱስትሪ ነው፡፡ ይሄ እንዴት ነው የሚተነተነው ብዙ ሃብቶች አሉ፡፡ ቅርስ፣ ተፈጥሮ ፣ባህል...... ወዘተ፡፡ እነዚህን ወደ ልማት ስናሽጋግራቸው ሥራ ፈጠራ ቱሪስቶች ወይም የጎብኝዎች መምጣትና የማህበረሰቡ ተጠቃሚነት ማለት ናቸው፡፡ ይህ ተቋም ደግሞ የሆስፑታሊቲ ስልጠና የሚሰጥበት በመሆኑ የምሰራው 50 ፐርሰንት ስራ እዚህ ነው፡፡

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ፡- ሆቴልና ቱሪዝም ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ውስጥ የቦርድ ሰብሳቢ ሆነው እንደሚያገለግሉ ይታወቃል፡፡ እርስዎ የቦርድ አካል ከሆኑ

በኋላ ምን አይነት ለውጦች መጥቷል ይላሉ?

ዶ/ር ሙልጌታ፡- እንግዲህ ለውጥ አዝጋሚ ነው፡፡ የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት ትምህርት ቤት እንደመሆኑ መጠን በለውጥ ላይ ነው፡፡ ለውጥ ሲባል የትምህርት ጥራትና የተማሪዎች ቁጥር ከግምት ውስጥ ስናስገባ በዚህ ተቋም ይህን ሁለት ነገር አያለሁ፡፡ ትንሿ CTTI አሁን ግዙፍ CTTI ሆናለች፡፡ የተማሪዎች ቁጥር ከዳታ ማግኘት ይቻላል፡፡ ዋናው ጉዳይ ጥራቱ ነው፡፡ ተቋሙ በተካታታይ አካሄድ ወጥነት ያለው ስልጠና፣ የጥናትና ምርምር አገልግሎቶችን ተደራሽ በማድረግ ሰፊውን ማህበረሰብ በማገልገል ላይ ላቅ ባለ ደረጃ ለመገምገም በቅቷል፡፡

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ፡- በመጨረሻም ዘላቂነት ያለው ቱሪዝም እንዲኖር መሰራት አለበት የሚሉት ነገር ካለና አያይዘውም ተቋሙ ማድረግ አለበት የሚሉት ካለ?

ዶ/ር ሙልጌታ፡- እንግዲህ በኢትዮጵያ ቱሪዝምና መስተንግዶ እንዲሁም ልማትን በተመለከተ እንደ ሀገር፣ እንደ ዜጋ ደፍረን የማንግባባበት ነገር አለ በየኮንፍረሱ የምናየው ቱሪዝሙንና መስተንግዶውን ስናስብ ሃገር እንደሚሸረሽር በህላችንን እንደሚያጠፉ በጥርጣሬ አይን ማየቱ አለ፡፡ ሁለተኛ ቱሪዝም ሲባል የኢኮኖሚ ጥገኝነት የሚመስላቸው አካላት አሉ፡፡ ይኼ ብዙ ይነገራል፣ ነገር ግን ሰፋ አድርገን ብናየው የማን ሀገር ነው የኢኮኖሚ ጥገኛ የሚሆነው? ያደጉት ሀገራት ባህላቸውም ሲሸረሸር አናይም፣ የኢኮኖሚ ጥገኛም አልሆኑም፡፡ በርካታ የአፍሪካ ሀገራትን መየት ይቻላል፡፡ ሌሎችም ኤዢያ፣ ላቲን አሜሪካ ብንወስድ አንዳቸውም የቱሪዝም ተጠቂ አልሆኑም፡፡ ያደረጉት ነገር ህዝባቸው በሚገባ መልኩ ስለ ቱሪዝም በሰፊው ያስተምራሉ፡፡ በመጨረሻም ግዴታውንና ጥቅሙን የሚያውቅ “informed” ማህበረሰብ ስለገነቡ ነው፡፡

ስለዚህ ሁሉም በተሰማራበት መስኩ የድርሻውን እየተወጣ ቱሪዝምና መስተንግዶን ጥቅም እንደ ሃገር ማስተማር ከቻልን ይሄ የከበበን እንቅፋት





የሆነብንን ነገር አስወግደን ያሉንን ታሪካዊ ቅርሶች ተጨባጭና የማይዳሰሱ ቅርሶች ባሉን ምሁራንና ተመራማሪዎች ህብረተሰባችንን በማስተማር ደረጃውን(standard) የጠበቀ ዓለም ዓቀፋዊ አገልግሎቶች መስጠት ይጠበቅብናል፡፡

ሆ.ቱ.ሥ.ማ.ኢ፡- ውድ ጊዜዎትን ሰውተው ለሰጡን ቃለመጠይቅ በመጽሔት ዝግጅቱና በተቋሙ ስም አመሰግናለሁ!

ዶ/ር ሙልጌታ፡- እኔም አመሰግናለሁ!

## የሁነት ቱሪዝም እና ፋይዳዎቹ

ቱሪዝም ራስን ለማደስ አልያም ለሌላ ጥቅም የሚደረግ ከተለመደው የመኖሪያ ቦታ በመውጣት ከ24 ተከታታይ ሰ ዓታት በላይ ከ1 ዓመት በታች የሚቆይ የጉዞ ዓይነት ነው። ቱሪዝም በተለያዩ ምክንያቶች የሚደረጉ የንግድ፣ ክብረ በዓላትና የተለያዩ ዝግጅቶች ፣የጤና፣ የትምህርት፣ የኃይማኖትና የመሳሰሉ ሃገር አቀፍና የዓለም አቀፍ ጉዞዎችን ያካትታል፡፡

ከነዚህ ምክኒያቶች በመነሳትም የቱሪዝም አይነትን በብዙ አይነት ልንከፋፍል እንችላለን፡፡ ከዚህ ውስጥም የሁነት ቱሪዝም (Event Tourism) አንዱና ዋነኛው ነው፡፡

የሁነት ቱሪዝም (Event Tourism) አንድ ዓላማን ለማሳካት በተወሰነ ቦታና ጊዜ የሚዘጋጁ ዓመታዊ በዓላት፣ ኮንፍረንሶች፣የውይይት መድረኮችና ሌሎችም መሰል ዝግጅቶችን የሚያካትት የቱሪዝም አይነት ነው፡፡ በሁነት ቱሪዝም (Event Tourism) ውስጥ እነዚህንና የመሳሰሉ ጉዞዎችን በማሳካትና በማዘጋጀት ለተጓዡ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ለራሳቸውም ትልቅ የስራ ዕድል ሆኖ የሚገለገሉበት የተለያዩ ድርጅቶችና ግለሰቦች ይገኛሉ፡፡ ከዚህም ውስጥ በሀገር ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ የትራንስፖርት አቅራቢ ድርጅቶች፣ የአስጎብኚ ድርጅቶች፣ የተለያዩ ማረፊያ፣የምግብና መጠጥ (Accomoda-

tion) አቅራቢ ድርጅቶች ፣ የጉዞ ወኪሎች፣ የአስጎብኚ ባለሙዎችና ሌሎችም አካላት ይገኙበታል፡፡

በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሁነት ቱሪዝም (Event Tourism) ከፍተኛ ድርሻ ያለውን ገቢ እንደሚያስገኝ የተለያዩ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሀገራችንም ከዚህ ዘርፍ በየዓመቱ ከሚደረጉ ዓለምዓቀፍ ስብሰባዎች፣ ኮንፍረንሶች፣ ኮንግሬሶች፣ የውይይት መድረኮችና አጠቃላይ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ቀላል የማይባል ገቢ እንደሚገኝና ለብዙ ሰዎችም የስራ ዕድልን እንደሚፈጥር እሙን ነው፡፡

የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩትም የሚያሰለጥናቸውን ሰልጣኞች በተቋሙ የቆይታ ጊዜያቸው ወቅት ያገኙትን የሁነት አከባበር እውቀት ወደ ተግባር የሚቀይሩበትን ዘዴ ለማሳየት፣ በተቋሙና ከተቋሙ ውጭ ያሉ ማህበረሰብን በቱሪዝም ኢንዱስትሪ ግንዛቤ ለመፍጠርና ለማጎልበት እንዲሁም በተቋሙ ዋና ዋና ተግባርና ሃላፊነቶች ዙሪያ ግንዛቤ እንዲያገኙ ለማድረግ በየዓመቱ የቱሪዝምና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት (Tourism and Hospitality week) ያከብራል፡፡

ተቋሙ የቱሪዝምና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንት (Tourism and Hospitality week) ከ2005 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ዝግጅቶች እያተከበረ ይገኛል፡፡ በነዚህ የሁነት ጊዜያትም በሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ስልጠናቸውን የሚከታተሉ ሰልጣኞች በየትምህርት መስካቸው የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናሉ፡ ፡ በሆቴል ዘርፍ የተለያዩ የምግብ ዝግጅት ስራዎችን ሰርቶ የሚያሳዩ ሲሆን በቱሪዝም ዘርፍ ደግሞ ሁነቱን በማደራጀትና በማስተባበር ለሁነት ቱሪዝም የሚያስፈልጉ ቅድመሁኔታዎችን እንዴት እንዴት እንደሚያዘጋጁ የሚረዱበት ነው፡፡ በዚህም አዲስ መልክ በዓለምአቀፍ ደረጃ እየተዋወቀ የመጣውን የስብሰባ፣የማበረታቻ፣ጉባኤና ሁነት (MICE) ዘርፍን በተግባር እንዲማሩት ያደርጋል፡፡

ልክ እንዳለፉት አምስት ዓመታትም የሆቴልና ቱሪዝም ስራ ማሰልጠኛ





ኢንስቲትዩት ዘንድሮም (በ2010 ዓ.ም) 6ኛውን ቱሪዝምና እንግዳ ተቀባይነት ሳምንትን (Tourism and Hospitality week) በግንቦት ወር ውስጥ ያከበራል፡፡

በሁነቱ ላይ የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትም፡-

* የእግር ጉዞ
* ባህላዊ ትዕይንቶች
* 7ኛው ዓመታዊ ሀገራዊ የጥናትና የምርምር ጉባኤ
* ኤግዚቢሽን
* ባህላዊና ዘመናዊ ውዝዋዜ ውድድሮች
* የእግር ኳስ ጨዋታና ሌሎች ስፖርታዊ ውድድሮች፤
* የቁንጅና ውድድሮች
* የቱሪዝም አይዶልና መዝናኛ ውድድሮች
* የምግብና መጠጥ ውድድሮች
* በተለያዩ ቋንቋዎች የሚደረግ የአስጎብኚ ውድድሮች፣
* የውጭ ምግብ ዝግጅት፤ የፔስትሪ፤ መስተንግዶ፤ ኮክቴል፤ አትክትልና ፍራፍሬ እና የባህላዊ ምግብ ዝግጅት ጥበብ ውድድሮች፤
* በተማሪዎች መካከል የሚደረግ ድንገተኛ የጥያቄና መልስ ውድድር
* የማበረታቻ ጉብኝት ፕሮግራም
* የምግብ አሰራር ጥበብ እና የክህሎት ውድድሮች (ምግብ ማዘጋጀት)
* የፍራፍሬ ምግቦች ዝግጅት ጥበብና ክህሎት ውድድር
* የአስተናጋጅነት ሙያ ጥበብና ክህሎት ውድድር
* የባርማን ሙያ ክህሎት ውድድር
* የኮክቴል ዝግጅት ውድድር
* የዳቦና ጣፋጭ ምግቦች ዝግጅት ውድድር
* የቱሪዝም እና አካባቢያዊ ሻምፓኝ
* የምስጋናና ሰርተፊኬት ስነ-ስርዓት እና ሌሎችም
* የምስጋናና ሰርተፊኬት ስነ-ስርዓት እና ሌሎችም














**Event Tourism and Its Impacts**

Tourism is defined as travel away from the traveler's normal place of residence and is much more than just leisure travel. It encompasses travel for a range of reasons such as business, festivals and events, health, education and religion. It includes both domestic and international travel and involves the consumption of a wide range of goods and services provided by transport and tour operators, travel agencies, accommodation providers, theme parks and attractions, tour guides, sporting, entertainment and arts venues, museums and historical sites, restaurants, cafes and clubs. Increasingly tourism operators are choosing to operate specialized tourism products, and term such as "Event Tourism" is regularly used.

Event Tourism is a systematic planning, development, and marketing of festivals and special events as tourist attractions, image-makers, catalysts for infrastructure and economic growth, and animators of built attraction.

Tourism management deals with tourism development based on analyzing the behavior and motivation of all kinds of tourists. On the other hand, event management deals with event marketing, design and managing of an event. Moreover, it tries to understand the event experiences and to manage them. Hence, event tourism is in the middle of the two sectors. In other words, event tourism aims at full exploitation of the capabilities of events in order to achieve tourism development of host communities.

An event can be described as a public assembly for the purpose of celebration, entertainment, education, or marketing and they can be either planned or unplanned.

**Roles of Event Tourism**

When we see the roles of such events, there are about 5 main tourism roles of events. Any one or all of these roles can be important for a community or destination, and event managers should evaluate how their events can make a positive contribution or tap into tourist markets.

**1. Events and Place Marketing**

Place marketing provides a framework within which events and event tourism find multiple roles, as image-makers, quality of life enhancers and tourist attractions. More traditional approaches to economic development stressed industrialization, provision of physical rather



የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
Catering and Tourism Training Inistitute

than cultural infrastructure, and downplayed the economic value of tourism.

One key feature of place marketing is its attention to cultivating a positive image. Thus, events produced or assisted by economic development departments, Mayor's offices, tourist agencies or convention and visitor bureaus all must attract media attention, portray the place in the best possible light.

**2. Events as Attractions**

Although many tourism organizations stress international tourism, there is no doubt that most festivals and events are dependent on local and regional audiences. But whether events are true tourist attractions or a reason for visitors already in an area to stay longer, they can have tourism value. Events can have the effect of keeping people and their money at home, rather than traveling outside the region. Event "drawing power" or "attractiveness" to tourists. A particular concern is the spreading of tourist demand:

(1) Over time (to overcome the tourist seasonality problem);

(2) In space (to spread demand throughout a country or region).

**3. Events as Image Makers**

Major events can have the effect of shaping an image of

the host community or country, leading to its favorable perception as a potential travel destination. With global media attention focused on the host city, even for a relatively short duration, the publicity value is enormous, and some destinations will use this fact alone to justify great expenditures on attracting events. Moreover, negative images can be turned into positive ones by organizing festivals and commemorations of the event. It is restricted the natural disasters and entails the risk of stirring up unhappy or controversial memories.

**4. Events as Catalysts**

Events, such as World's Fairs and Olympics, have been supported by host governments in large part because of their role as catalysts in major redevelopment schemes.

Major events tend to attract investment into the hospitality sector, especially hotels and restaurants.

Sport events generally lead to new or improved facilities which can be used to attract events in the future. In this way a community can use the event to realize a "quantum leap" in its tourism development, accelerating growth or jumping into a higher competitive category.



የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
Catering and Tourism Training Inistitute

**5. Events as Animators**

Resorts, museums, historic districts, heritage sites, archaeological sites, markets and shopping centers, sports stadiums, convention centers, and theme parks all develop programs of special events. Built attractions and facilities have everywhere realized the advantages of "animation" - the process of programming interpretive features and/or special events which make the place come alive with sensory stimulation and attractive atmosphere.

The potential benefits of animation through events are of major importance to facility and attraction managers:

(1) To attract people who might otherwise not make a visit because they perceive the facility or attraction itself to be uninteresting

(2) To encourage repeat visits by people who might otherwise think that one visit is enough

(3) Relatives who might otherwise not include certain attractions on their list of things to do

(4) To attract publicity for the site or facility, including the highlighting of historical events associated with the site

(5) To encourage longer stays and greater spending

(6) To target groups for special functions

# የመዝናኛ ገፅ

የህዳሴ ግድብ የፐዝል ጨዋታ
በህዝብና አለምዓቀፍ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ
የታችኞቹንና የላይኞቹን የአባይ ተፋሰስ ሀገራትን ስም ፈልግ/ጊ

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዩ | ቃ | ዳ | ን | ቡ | ብ | ዲ | ዩ | ን | ን |
| ቃ | ዩ | ዋ | ጎ | ግ | ኢ | ጋ | ያ | ጋ | ሩ |
| ን | ዲ | ብ | ብ | ሩ | ን | ዲ | ጵ | ኤ | ን |
| ዳ | ኢ | ጵ | ት | ዳ | ራ | ኬ | ብ | ራ | ያ |
| ሩ | ን | ዳ | ሱ | ብ | ን | ን | ኒ | ዳ | ቡ |
| ጵ | ግ | ብ | ጵ | ያ | ግ | ዋ | ጵ | ብ | ት |
| ኬ | ቡ | ብ | ኒ | ጵ | ያ | ኤ | ሩ | ግ | ን |
| ደ | ኮ | ዛ | ራ | ዮ | ር | ን | ያ | ዛ | ን |
| ጵ | ን | ብ | ዳ | ት | ቡ | ዩ | ኒ | ቡ | ብ |
| ቃ | ጎ | ዛ | ራ | ኢ | ን | ን | ዳ | ሩ | ዳ |



የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
Catering and Tourism Training Inistitute

## WHY ETHIOPIA IS LAND OF ORIGINS?

## A UNIQUE TOURISM DESTINATION

Ethiopia is a country with one of the richest histories on the African continent, a land of contrasts and surprises, of remote and wild places, home to friendly people who are descended from some of the world's oldest civilizations.

## 10 REASONS TO VISIT

1. Cradle of human kind: come to see Lucy, the oldest and most famous of all early hominids.
2. Find out where the original Ark of the Covenant is kept in Axum and learn about the story of the Queen of Sheba.
3. Feel the mysticism of the medieval Rock Hewn Churches in Lalibela.
4. Learn about the castles of the Ethiopian kings in Gondar, inspired in Europe, unique in Africa.
5. Take a high altitude trek in the Simien Mountains, home to the Gelada Baboon and other endemic species.
6. Visit the region of Kaffa, origin of coffee.
7. Discover the lower Omo Valley cultures: untouched by civilization.
8. Explore the Danakil Depression with colorful geothermal features and climb the active Ertale volcano to experience the magnificent boiling lava lake.

9.Wander around the walled city of Harar, with over 80 mosques, and townhouses with unique interior decoration.

10.Enjoy the cultural life and entertainment of Addis Ababa, the diplomatic capital of Africa, and participate in the Great Ethiopian Run.

## FACTS ABOUT ETHIOPIA?

Ethiopia is Africa's oldest polity (state).It is the only country in Africa never to have been colonised.

It is mentioned 44 times in the Old Testament.

* 1st – 7th century AD – Aksumite Empire – Major maritime power, one of the most important and advanced civilisations of its time, creating the roots of modern Ethiopia and establishing Christianity as the official religion (until 1974).
* 7th century AD – the first migration (Hijra) of the Companions and relative of the Prophet Muhamed to Ethiopia celebrated the birth of freedom of expression and beliefs.
* 12th century AD – the amazing and astonishing rock hewn churches of Lalibela (know as the second Jerusalem) were created.
* 17th century – Gondar was established as the capital of Ethiopia, and is notable for its medieval castles and churches. The city's unique Imperial compound contains a number of castles built between 1632 and 1855 by various Emperors who reigned during this period.
* 1889-1913 – Emperor Menelik II decisively defeats Italy at the historic battle of Adwa in 1896 foiling its colonial ambitions. He completes the process of unification and modernisation started by some of his predecessors.



የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
Catering and Tourism Training Inistitute

* 1930 - Haile Selassie (the last Emperor) was crowned, Five years later fascist Italy invaded Ethiopia and occupied it for the following five years. Yet, Ethiopian patriots put up a stiff resistance throughout the occupation period. With Italy's declaration of war in 1940 against Britain and the allied powers, British officers and troops decided to attack Italy at its Achilles hill where Ethiopian patriots had already weakened it. Thus, they helped liberate Ethiopia.
* 1974-1991 - Haile Selassie was overthrown by a socialist-inspired revolution in 1974 and by the military regime which ruled until 1991 under Mengistu Haile Mariam.
* 1991-2016 - The country's first democratic republic was installed creating a peaceful country where 80 nations and nationalities and peoples, followers of different religions live in peaceful coexistence and others...

## GEOGRAPHY

* Situated on the Horn of Africa with a surface area of 1.2 million km2.
* Ethiopia is twice the size of Texas, and five times larger than the UK.
* Approximately 70% of Africa's mountains are in Ethiopia. Two thirds of Ethiopia rises high above Northeast Africa's lowlands to form part of the Great Rift Valley, a geographical feature that can be seen from the moon.

* Population: 92 million.

* The country comprises over 80 ethnic groups.

## CLIMATE

Ethiopia is located in Eastern Africa and due to its varied landscape it has three distinctive climate zones:

* Qolla (Hot zone) South East/North East Lowlands. Below 1830m, average annual temperature 27oC, average annual rainfall 510mm.

* Woina Dega (Mild zone) Central Highlands. Elevation of 1830-2440m, average annual temperature 22oC, average annual rainfall 510mm-1530mm.

* Dega (Cool zone) – Central Northwestern Plateau and Harar. Above 2440m, average annual temperature 16oC, average annual rainfall 1270-1280mm.

## SEASONS

* June/July/August. Rainy season.

* September/October/November. Harvest season.

* December/January/February. Dry season sometimes with cold evenings in January.

* March/April/May. Occasional showers. May is the hottest month.





## FESTIVALS

Below are the most important festivals and holidays in Ethiopia, which are celebrated enthusiastically and which tourists may wish to center their holidays around, being such colorful occasions.

| Types of Festivals | |
|---|---|
| January 7 | Ethiopian Christmas Day |
| **January 20** | Epiphany (Timket) |
| March 2 | Adwa Victory Day |
| **April 29** | Ethiopian Good Friday |
| **May 1** | Ethiopian Easter Sunday |
| May 1 | International Labor Day |
| May 5 | Patriots Day |
| May 28 | Derg Downfall Day |
| July 6 | Eid al-Fitr |
| September 12 | Ethiopian New Year |
| September 23 | Eid al-Adha |
| September 28 | Finding of the True Cross (Meskel) |
| December 7 | Nations and Nationalities Day |
| December 12 | Birth of Prophet Mohammed |

2016 is a Leap Year; 2017, 2018 and 2019 will have different days/ dates for some festivals.

# ከፎቶ አልበማችን



የሆ.ቱ.ሥ.ኢ የቀድሞ ሰልጣኞች ህብረት ሲመሰረት



ሰልጣኞች በጎንደር ጉብኝት ሲያደርጉ







ሰልጣኞች በአቡነ የማታ ትምህርታዊ ጉብኝት ሲያደርጉ



ሰልጣኞች በቅ/ላልይበላ ትምህርታዊ ጉብኝት ሲያደርጉ



ሰልጣኞች በስሜን ፓርክ በትምህርታዊ ጉብኝት ላይ



የባሌ ተራሮች



የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
Catering and Tourism Training Inistitute



የተቋሙ ሰራተኞች በኦሞ ወንዝ በጉብኘት ላይ



ተቋሙ መምህራን በጉብኘት ላይ


Hilton
HILTON WORLDWIDE
BE EXTRAORDINARY!
www.hiltonworldwide.com/careers
CONRAD
HILTON WORLDWIDE
የሆቴልና ቱሪዝም ሥራ ማሰልጠኛ ኢንስቲትዩት
Catering and Tourism Training Inistitute